# የተንኰል ምንጩ መስፍን  ወልደ ማርያም።

መስፍን ወልደ ማርያምን ላስታውስህ የምፈልገው ነገር ቢኖር ከተንኮል ሥራዎችህ አለ መላቀቅህ ያስገርመኛል። ሕልምህ ተንኮልን ሲያወጣና ሲያወርድ የሚያድር ይመስለኛል። ከተማሪነትህ ግዜ ጀምሮ ባሳለፍካቸው ዘመናት ሁሉ፣ ለተንኮል ሥራ የተዘጋጀህ በመሆንህ፤ ለሀገራችን ታጋድሎ ያደረጉትን፣ በቅንነትና በታማኝነት አገራቸውን ያገለገሉትን ኢትዮጵያውያን አባቶችና ታዋቂ ባለ ሥልጣኖች በመደዳ ስትወቅስና ሳትሰለች ትናገር ነበረ። የአገሪቱን ሀብት እየዘረፉ ወደ ውጭም የሚያሸሹ አድርገህ ስትወነጅላቸው ቆይተሃል። ለተማሪዎችህም ለአገር የሚጠቅሙ ዕውቀት አስተምረህ ለሀገራቸው ታምኝና ፍቅር እንዲኖራቸው በማድረግ ፈንታ፤ ተቃራኒው ያንተን ፍልስፍና የሚያንጸባርቅ የተንኮል ሥራዎችን እንዲያራምዱ አድርገሃል። ይህ ተግባርህ ያስከተለው ለአገራችን ጥፋት፣ ጀግኖች አባቶቻችንና አኩሪ የነበሩ የፖለቲካ ዐዋቂዎችን፣ ወጣቶችን፣ ከፍተኛ የጦር መኰንኖችን ከጓደኛህ በረከት ሀብተ ሥላሴ ጋር ሆነህ እንዲገደሉ አድርገሃል። እንዲገደሉ የተናገራችሁትን ማበረታቻ ጭካኔ ሥራችሁንም መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ለወሰደው ዕርምጃ እራሱ አረጋድጧል። በዚህ በምንጓዝበት አሰቃቂና የመከራ ዘመን ቀስተ ደመና የተባለውን የፖለትካ ድርጅት ካቋቋምክ በኋላ በተለመደው ተንኮልህ ከመላው የኢትዮጵያ አንድነት የፖለቲካ ድርጅትና ከሌሎችም ጋር እንዲዋሃድ አደረግህ።ቆይተህም ለማፈራረስ ተዘጋጅተህ ስለነበረ፣ በቅንጅት ላይ የፈጸምከውን ችግር ትረሳው ይሆን?። የችግሩ መንስኤ አንተ ተንኰለኛው እንደ ሆንክ አብረውህ የነበሩት ምሁራን ያውቁታል።

መስፍን፣ አንተ ማነህ?። ለኢትዮጵያ ምን ቁም ነገር አስተዋጽዎ አደረግህ?። ጅዖግራፊ ከማስተማርህ ሌላ በደርግ ዘመን ለአገር ጥፋት ለአባቶችና ታዋቂ ባለ ሥልጣኖች፤ ለወጣቶችና ለከፍተኛ የጦር መኰንኖች መጨፍጨፍ ምክንያት ሆነሃል። አሁን ደግሞ በማይታመን ሥውር ዘዴህ ለግማሽ ጐንህ ወያኔ የግፍ ሥራ ድጋፍ ሰጭ እንጂ ኢትዮጵያ አንድነቷ ተጠብቆና ተከብሮ እንዲኖር ባለ መፈለግ ዐመፅን ታፈቅራለህ። ነገሮችን ወዲያና ወዲህ የምተወሳስብ ነህ።

በዐፄ ኃይለ ሥላሴ  ዘመነ መንግሥት የተንኮል ሥራህና ዐመፅ አድራጐትህ ታውቆ፤ ጠባይህን ማረም ትችል እንደሆነ ተብሎ በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት በአውራጃ አስተዳዳሪነት እንድትዛወር ተደረገ። በወቅቱም አልቅሰህ በመምህርነትህ እንድትቆይ ያቀረብከው የይቅርታ ልመናህን አስታውስ። አንተ ግን ቂምህን ሳትረሳ እነዚያ የረዱህን አባቶች በጥይት ሲደበደቡ ሥቀሃል። አልቆረቆረህምና ታሪክ ያስትውስሃል።

ዛሬ ይህን ሁሉ ሐተታ ሊያናግረኝ የቻለው ትላቁን ደራሲ ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤልን ከዐረፉ በኋላ አላስተኛ በማለትህ ነው። ሁሉን ዐውቃለሁ ባይ ስለሆንክ፣ ስለ ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል ማንነት ብዙ ሌሎች ነገሮች የምትገልጻቸው ሳታጣ፣ ለትምህርት አገልግሎት ባዘጋጁት መጽሐፍ አንተም፣ እኔም፣ ሌሎችም በተማርንበት፡ "ታሪክና ምሳሌ" መጽሐፍ የጻፉትን ግጥም ሰምና ወርቁን መለዬት አቅቶህ ወይም ያልተረዳኸውን ቃል ለመጥቀስ የመረጥኸው "የኢጣልያን ፋሺስት አገልጋይ የነበሩ" በማለት ታላቅ ሥራቸውን ዋጋ ቢስ ለማድረግ መሞከርህ የሚያሳፍር ነው። ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል የውስጥ አርበኛና በርከት ያሉ የውጭ አገር ቋንቅቅዎችን አቀላጥፈው ተናጋሪ የነበሩ አኩሪ ኢትዮጵያዊ ናቸው። ያንተስ አባትና እናት በፋሾስት አገዛዝ የት ነበሩ?። ምንስ ይሠሩ ነበር?። ስለ መሬት ልማትና ጥፋት መናገር ከፈለግህ የክቡር አቶ ከበደ ሚካኤልን ስም መጥቀስ ለምን አስፈለገህ?። በአሁኑ ግዜ በኢትዮጵያ ተደርጐ የማያውቅ መሬት ወያኔዎች ለባዕድ ሲቸረችሩ የተመለከትከውን ጠቅሰህ ለምን ወያኔዎችን ከመውቀስ የተቆጠብክና እኒህን የተከበሩ ሰው ለመዝለፍ ተነሣህ?። ልማድህ ስለሆነ ምን ይደረግ......። ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል ለአገር አኩሪ የሆኑ ብዙ መጽሐፎች ኢትዮጵያውያን እንዲጠቀሙበት አቅርበዋል። አንተም አትከድም። ታዲያ ዕውነቱን በመናገር ፈንታ ለምን ይህን የመሰለ ወራዳ ነገርህን ለሕዝብ ለማሳወቅ ሞከርክ?። ታሳዝናለህ። ሳታውቅ ለማዋረድ አትቸኩል። ከሚገርመኝ ነገር ሁሉ ይህ የተጠናወተህ ሰይጣናዊ የተንኮል አስተሳሰብህ መቼ ትላቀቀው ይሆን?። ለጂዖግራፊ ዐዋቂነትህ የፕሮፌሰር ማዕርግ ተቀዳጅተሃል። ከዚያ ሌላ ለተንኮል ሥራህስ?። በዕውነት ዕውቀትህን ገለባ አታድርገው። በአካባቢህና በውጭ አገር ስደት የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን አብዛኛው በለውጡ አቅራቢያና ከዚያም ወዲህ የተወለዱ በመሆናቸው የአገራቸውን ታሪክ አያውቁም። የአገራቸውን ቀደምት ሁኔታ የማያውቁ የሚያደርጉት የጠፋቸው እነዚህን ኢትዮጵያውያን በምትነዛው አሳሳች ንግግርና ጽሑፍ ሳትመርዛቸው ቀናውን ነገር እንዲያውቁ ማድረጉ ይሻላል። ስለዚህም የተንኮል ሥራህን ብታቆም ጠቃሚ ነው። በአምላካችን ፋቃድ የሞቱትን በአንተና በጓደኞህ ገፋፊነት ያለ ፍርድ የተጨፈጨፉት ወገኖቻችንን በኃያሉ አምላካችን ፊት ይፋረዷችኋል። የግፍ ሥራ ሲፈጸም የሚያረካህ ስለሆነ ፈጣሪህን ታምን ይሆን?። ያጠራጥራል።

# የእግዚአብሔር ኃይል ሕዝቧንና ኢትዮጵያን ይጠብቃት።

ከሞገስ፡ታምሩ፣ሲልቨርስፕሪንግ።
For comment:- mogestameru@yahoo.com